## ለተከበራችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን
## እና የፀጋዬ ድህረ ገጽ ተከታታዮች በሙሉ ! ! !

## እንኳን ለሁለት ሺህ አንድ / 2001 / ዓ.ም. አዲስ ዓመት
## በሰላምና በጤና አደረሳችሁ! ! !

# እ ን ቁ ጣ ጣ ሽ ! ! !

አዲሱ ዓመት በግል፣ በቤተሰብ፣ በማህበርና በድርጅት ደረጃ ሀገራችን አሁን ካለችበት የጭንቆና ቀንበር፣ እንዲሁም ወገኖቻችን ከሚደርስባቸው የመከራና የሰቆቃ ኑሮ ተላቀው ነፃነት፣ ሰላም፣ እኩልነትና ብልፅግና የሰፈነባት ሀገረ - ኢትዮጵያን ለመመሥረት በምናደርገው የትግል መስክ ሁሉ አመርቂ ውጤት ለማስመዝገብ የምንችልበት የድል ዓመት እንዲሆንልን ልባዊ ምኞታችንን እየገለጽን፣

## ትውልድን በትውልድ፤ ዘመንን በዘመን የሚተካ
## የኢትዮጵያ ቅዱስ አምላክ፣

- በሰው ህሊና የማያስቡ፣ የወገን ፍቅር የሌላቸውና በወገን ስቃይ የሚደሰቱ የዘመናችን ባለሥልጣኖችና የአጋሮቻቸውን ኃይልና ጉልበት እንዲያዳክምልን፣

- የሀገርና የወገን ፍቅር እያቃጠለ ዕንቅልፍ ለነሳቸው እና በሚችሉት ሁሉ ለሚታገሉት ወገኖቻችን ኃይልና ጉልበትን ጨምሮ ጨማምሮ እንዲሰጥልንና ለአኩሪ ድል እንዲበቁ እንዲያደርግልን፣

- እነ ሆድ አምላኩና በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የሀገር ጥፋትንና የወገንን ስቃይ ላለማየት ፊታቸውን ላዞሩትም ሆነ አይተው እንዳላዩና ሰምተው እንዳልሰሙት ለሆኑት ሁሉ አስተዋይ ልቦናና ሰሚ ጆሮን እንዲሰጥልን፣

- ሀገራችንና ወገኖቻችን የድረሱልን ጥሪና ጩኸት ሲያሰሙ ለተኙት መንቃቱን እና አለን፣ ምን እናድርግ የሚል ምላሽ እንዲያሰጥልን፣

- የተበታተንነውን ኢትጵያውያንን በአንድነት ለሀገርና ለወገን ነፃነት በሚጠቅም ማህበርና ድርጅት ጥላ ሥር በየአለንበት አሰባስቦ በአንድ የትግል መሥመር እንዲያሰልፈልን፣

- የሃይማኖት መሪዎችና ታዋቂ ኢትዮጵያውያን በግልም ሆነ በጋራ ለሀገርና ለወገን ነፃነት በሚደረግ ትግል አጋርነታቸውን የሚገልጹበት፣ ያላቸውን ክብርና ሥልጣን እንዲሁም መድረክ ለሀገርና ለወገን ድኅነት በሚደረግ ትግል ለመስዋትነት እንዲያነሳሳልን፣

- ለአዲሱ ትውልድ አዲሲቱን ነፃና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባትና ለመምራት የሚያስችለውን ጥበብ፣ ፍቅር፣ አንድነት፣ ኃይልና ጉልበት እንዲሰጥልን ፣

ከልብ እንለምነዋለን። በእኛ በኩልም “ ትውልዳዊ ድርሻችንን እንወጣ “ ብለን በጀመርነው ሥራ ሁሉ አቅማችን የፈቀደውን አስተዋፅኦ ለማበርከትና ለፍትህና ለነፃነት ትግል ከተሰለፉት ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ጎን በፅናት ለመቆም ቃል እንገባለን።

## መልካም አዲስ ዓመት
## መስከረም 1 ቀን 2001 ዓ. ም.
## የፀጋዬ ድኅረ ገፅ ዝግጅት ክፍል

http://www.tsegaye.ethio.info